# የMedicare ወጪዎችዎ ላይ እገዛ ያግኙ

ለእርስዎ ገንዘብ ሊያድኑልዎት የሚችሉ ፕሮግራሞችን ያመልክቱ

መጀመር



Medicare

## የMedicare ቁጠባ ፕሮግራም ገንዘብ ሊያድንልዎት ይችላል

የተወሰኑ የብቃት መስፈርቶችን ካሟሉ፣ ግዛትዎ የMedicare ፕሪሚየም ክፍያዎችዎን ለመክፈል ይረዳዎታል። በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ የMedicare ቁጠባ ፕሮግራም የMedicare ክፍል A (የሆስፒታል ኢንሹራንስ) እና ክፍል B (የህክምና ኢንሹራንስ) ተቀናሾችን፣ የጋራ ኢንሹራንስን እና የጋራ ክፍያዎችንም ሊከፍል ይችላል።

### የMedicare ቁጠባ ፕሮግራሞች 4 አይነቶች አሉ፦

1. ብቁ የMedicare ተጠቃሚ (QMB)
2. የተገለጸ ዝቅተኛ ገቢ ያለው የMedicare ተጠቃሚ (SLMB)
3. ብቁ ግለሰብ (QI)
4. ብቁ የሆኑ አካል ጉዳተኞች እና የሚሰሩ ግለሰቦች (QDWI)

ሲያመለክቱ፣ ግዛትዎ ለምን ዓይነት የMedicare የቁጠባ ፕሮግራም(ሞች) ብቁ እንደሚሆኑ ይወስናል። ለQMB፣ SLMB ወይም QI ፕሮግራም ብቁ ከሆኑ፣ ለMedicare የመድሃኒት ሽፋን (ክፍል D) ወጪ እንዲሸፈን ተጨማሪ እርዳታ ለማግኘት በራስ-ሰር ብቁ ይሆናሉ።

ተጨማሪ እርዳታ የMedicare ፕሮግራም ሲሆን፣ ዝቅተኛ ገቢና ሀብት ያላቸው ሰዎች የMedicare የመድሃኒት ሽፋን ፕሪሚየሞችን፣ ተቀናሾችን፣ የጋራ ኢንሹራንስን እና ሌሎች ከኪስ የሚከፈሉ ክፍያዎችን ለመክፈል ይረዳል። ለተጨማሪ መረጃ የሚከተለውን ይጎብኙ Medicare.gov/basics/costs/help/drug-costs።

## ለMedicare ቁጠባ ፕሮግራም ያመልክቱ

ለግዛትዎ የሕክምና እርዳታ (Medicaid) ቢሮ ይደውሉ ወይም ማመልከቻ ቅፅ ይሙሉ። ገቢዎ ወይም ሀብትዎ በሚቀጥለው ገፅ ከተዘረዘሩት የፌዴራል ገደቦች ከፍ ቢሆኑም፣ በግዛትዎ ውስጥ ለእነዚህ ፕሮግራሞች አሁንም ብቁ ሊሆኑ ይችላል። የግዛትዎን Medicaid ቢሮ ስልክ ቁጥር ለማግኘት Medicaid.gov/about-us/where-can-people-get-help-medicaid-chip ይጎብኙ። እንዲሁም ለግዛት Medicaid ቢሮ የእውቂያ መረጃ ለማግኘት 1-800-MEDICARE (1-800-633-4227) መደወል ይችላሉ። የTTY ተጠቃሚዎች ወደ 1-877-486-2048 ሊደውሉ ይችላሉ።

**ብቁ መሆንዎን ለማወቅ ብቸኛው መንገድ ማመልከት ነው።**

## 3 አስፈላጊ ጥያቄዎች

እነዚህ ጥያቄዎች ላይ "አዎ" ብለው ከመለሱ፣ በግዛትዎ ውስጥ ለMedicare የቁጠባ ፕሮግራም ብቁ መሆንዎን ለማወቅ ወደ ግዛትዎ የMedical እርዳታ ቢሮ ይደውሉ።

1. **የMedicare Part A አለዎት? ወይስ ለመቀበል ብቁ ነዎት?** እርግጠኛ ካልሆኑ፣ በቀይ፣ ነጭ እና ሰማያዊ የMedicare ካርድዎ ላይ ይመልከቱ። ካርድ ከሌለዎት፣ ወደ 1-800-MEDICARE ይደውሉና የምትክ ካርድ በፖስታ እንዲላክልዎት ይጠይቁ። የTTY ተጠቃሚዎች ወደ 1-877-486-2048 መደወል ይችላሉ።
2. **የእርስዎ የ2026 ገቢ በቀጣዩ ገፅ ላይ የተዘረዘሩትን ገደቦች ያህል ወይም ከዚያ በታች ነው??** በሰንጠረዡ ውስጥ ያለው መረጃ Medicare.gov/medicare-savings-programs ላይ ይገኛል። ከስራ የሚያገኙት ገቢ ካለ፣ ገቢዎ ከእነዚህ ገደቦች በላይ ቢሆንም ለእነዚህ ፕሮግራሞች ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።
3. **አነስተኛ ሀብት አለዎት?** በአብዛኛው ግዛቶች፣ ንብረቶችዎ ከተወሰነ መጠን በታች ሊሆኑ ይገባል።

   የሚቆጠሩ ሀብቶች በቼኪንግ ወይም በቁጠባ መለያ ውስጥ ያለ ገንዘብን፣ አክሲዮኖችን፣ እና ቦንዶችን ሊያካትቱ ይችላሉ። በየትኛውም ጊዜ ሀብቶችዎን ሲቆጥሩ፣ ቤትዎን፣ አንድ መኪና፣ የቀብር መሬት፣ ለቀብር ወጪዎች እስከ $1,500 ድረስ (ይህን ገንዘብ ወደጎን ከተዉ)፣ የቤት ዕቃዎች ወይም ሌሎች የቤትና የግል እቃዎችን አያካትቱ።

አንዳንድ ግዛቶች ማን ብቁ እንደሚሆን ሲወስኑ የገቢ ወይም የሀብት አይነቶችን ወይም የተወሰኑ መጠኖችን አይቆጥሩም። የገቢ እና የሀብት ገደቦች በየዓመቱ ሊለዋወጡ ይችላሉ።

## የ2026 የፕሮግራም የገቢ ገደቦች

| የMedicare ቁጠባ ፕሮግራም | የግለሰብ ወርሃዊ የገቢ ገደብ* | የተጋቡ ባል እና ሚስት ወርሃዊ የገቢ ገደብ* | የእርስዎን የሚከተለውን ለመክፈል ይረዳል |
|---|---|---|---|
| **QMB** | $1,350 | $1,824 | የMedicare ክፍል A እና ክፍል B ፕሪሚየሞች እና ሌሎች ወጪዎች (እንደ ተቀናሽ ክፍያዎች፣ የጋራ ኢንሹራንስ እና የጋራ ክፍያዎች) |
| **SLMB** | $1,616 | $2,184 | የMedicare ክፍል B ፕሪሚየሞች (ብቁ ለመሆን ክፍል A ሊኖርዎት ይገባል) |
| **QI** | $1,816 | $2,455 | የMedicare ክፍል B ፕሪሚየሞች (ብቁ ለመሆን ክፍል A ሊኖርዎት ይገባል) |
| **QDWI** | $5,405 | $7,299 | የMedicare ክፍል A ፕሪሚየሞች ብቻ |

*የገቢ ገደቦች በአላስካ እና ሀዋይ ትንሽ ከፍ ይላሉ። ከስራ የሚያገኙት ገቢ ካለ፣ ገቢዎ ከእነዚህ ገደቦች የሚበልጥ ቢሆንም ለእነዚህ ፕሮግራሞች ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። አንዳንድ ግዛቶች ከፍተኛ የገቢ ደረጃዎች አላቸው ወይም ለQMB፣ SLMB፣ እና QI የገቢ አይነቶች ወይም መጠኖችን አያስቀምጡም።

## የ2026 የፕሮግራም የገቢ ገደቦች

| የMedicare ቁጠባ ፕሮግራም | የግል የሀብት ገደብ | የተጋቡ ባል እና ሚስት የሀብት ገደብ* |
|---|---|---|
| **QMB**<br>**SLMB**<br>**QI** | $9,950 | $14,910 |
| **QDWI** | $4,000 | $6,000 |

አንዳንድ ግዛቶች ከፍተኛ የሀብት ደረጃዎች አሏቸው ወይም ለQMB፣ SLMB እና QI ሀብትን አይቆጥሩም።

## ለበለጠ መረጃ

- የጤና እና የመድኃኒት ወጪዎችን ለመቀነስ መንገዶችን ለማወቅ Medicare.gov/basics/costs/help ይጎብኙ።
- ወደ 1-800-MEDICARE ይደውሉ እና ለእርስዎ የMedicare ፕሪሚየሞች ለመክፈል እርዳታ እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ይጠይቁ። የTTY ተጠቃሚዎች 1-877-486-2048 ሊደውሉ ይችላሉ።

Medicare

"ለMedicare ወጪዎችዎ እርዳታ ያግኙ" (“Get help with your Medicare costs”) የህግ ሰነድ አይደለም። ኦፊሴላዊ የMedicare ፕሮግራም ህጋዊ መመሪያ በተዛማጅ ሕጎች፣ ትእዛዞች እና ውሳኔዎች ውስጥ ይገኛል።

እርስዎ የMedicare መረጃን እንደ ትልቅ ህትመት፣ ብሬይል ወይም ኦዲዮ ባሉ ተደራሽ ቅርጸቶች የማግኘት መብት አለዎት። እንዲሁም ማንኛውም አይነት መድልዎ እንደደረሰብዎት ከተሰማዎት፣ ቅሬታ የማቅረብ መብት አለዎት። ለበለጠ መረጃ **Medicare.gov/about-us/accessibility-nondiscrimination-notice** ይጎብኙ ወይም ወደ 1-800-MEDICARE (1-800-633-4227) ይደውሉ። የTTY ተጠቃሚዎች 1-877-486-2048 ሊደውሉ ይችላሉ።

This product was produced at U.S. taxpayer expense.

CMS Product No. 10126-AMH (Amharic) • April 2026